# ኣዲስ መራጮች

VOTE 2024

## ኣዲስ መራጭ ኖትን? ኣትስጉ - እነኚህ እርምጃዎች ሂደቱን ያብራራሉ

## ወደ ምርጫ ጣብያዎ ይሂዱ

የሚመርጡት በተመደበልዎ የምርጫ ጣብያ ውስጥ ነው።ይህ ቦታ፡ ኣብዛኛውን ግዜ፡ በሚኖሩበት ኣካባቢ ነው። የምርጫ ጣብያዎን ለማወቅ mnvotes.govን. ይጎብኙ። ኣብዛኛዎቹ የምርጫ ጣብያዎች (እ.ኢ.ኣ) ከጥዋቱ ኣንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ክፍት ሁነው ይቆያሉ።(እንደ ፈረንጆች ኣቆጣጠር ደግሞ ከ7 am. እስከ 8 pm).

## ይፈርሙ ወይም ይመዝገቡ

ለመምረጥ ከተመዘገቡ፡ ስምዎ ከተመዘገቡ ሰዎች ዝርዝር ጋር ይገኛል። ከዚህ በውሃላ ማድረግ የሚያስፈልግዎ፡ ፊርማዎን ከስምዎ ጎን ማስፈር ብቻ ነው። ስሞን በሚፈርሙበት ግዜ፡ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ከሆነ፡ የመታወቅያ ወረቀት ማሳየት ኣያስፈልጎትም።

ከምርጫው ቀን በፊት ያልተመዘገቡ ከሆኑ፡ ኣሁን ያሉበትን የመኖርያ ቤት ኣድራሻ ማረጋገጫ ማሳየት ያስፈልጎታል። ለምሳሌ ወቅታዊ የሆነ የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድ፡ወይም የክፍለሃገሩ የመታወቅያ ወረቀት ማሳየት ይችላሉ። ወይም የቀድሞ ኣድራሻዎ ጋር ስዕሎ ያለበት የመታወቅያ ወረቀትና ወቅታዊ ኣድራሻዎ ያለበት የክፍያ ወረቀት ማሳየት ይችላሉ።

ምን ዓይነት የመታወቅያ ወረቀቶችንና ጽሁፎችን ለማምጣት እንደምትችሉ ዝርዝሩን ለማወቅ mnvotes.gov. ይጎብኙ

### የ2024 ቀናት

*የማጣርያ ምርጫ*
*ማክሰኞ፡ ነሃሴ 13 ቀን*

*በኣካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ*
*በፖስታ መምረጥ ወይም በኣካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 20ቀን እስከ ህዳር 4 ቀን*

*ለመምረጥ ተመዝገቡ*
*በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 15 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።*

*የምርጫ ቀን*
*ማክሰኞ ህዳር 5 ቀን*

ከበስተጀርባ ይቀጥላል...

# ኣዲስ መራጮች

VOTE 2024

...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ

## ምርጫ

የግል በሆነ ቦታ ይመርጣሉ፡ የመረጡት ምርጫ ሚስጥር ነው።እርሳስ ወይም ብዕር በመጠቀም ይምረጡ፡ ከምርጫዎ ኣጠገብ ያለውን ሳጥን ሙሉ በሙሉ ይምሉት።

ለእያንዳንዱ የስራ ቦታ ምን ያህል ዕጩዎችን እንደሚመርጡ የምርጫው ወረቀት መመሪያዎች ያስረዳሉ። ኣብዛኛውን ግዜ “ ኣንድ ብቻ ምረጡ” ይላል። ኣንዳንድ የቀበሌ መስርያ ቤቶች ከኣንድ የስራ ቦታ ይበልጥ ለምርጫ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

የቀረቡትን ምርጫዎች በሙሉ ባይሞሉም፡ የመረጡት ይቆጠርሎታል።

## የምርጫ ወረቀቶን ወደ ምርጫው ሳጥን ይውሰዱ

ከመረጡ ወይም ድምጾን ከሰጡ በውሃላ፡ የምርጫ ወረቀትዎን ምርጫ ቆጣሪ ሳጥን ውስጥ ይክተቱ። ወደ ቤትዎ ከመሄድዎ በፊት “በዛሬው ዕለት መርጫለሁ” የሚል ተለጣፊ ምልክት መውሰድ ኣይርሱ።

## በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ኣስቀድመው ለመምረጥ ለሚፈልጉ በሚሰጥ ወረቀት ኣስቀድመው ይምረጡ

ከዓርብ መስከረም 21 ቀን ጀምሮ ወደ ምርጫ ጣብያዎ በመሄድ ኣስቀድመው መምረጥ ይችላሉ። በኣካል ለማይገኙ መራጮች የሚሰጠው የምርጫ ወረቀት በፖስታ እንዲላክልዎ ማማልከት ይችላሉ። የምርጫ ጣብያዎ የት እንደሆነ ለማወቅና በኣካል ተገኝተው በዕለቱ ለመምረጥ ለማይችሉ ሰዎች የሚላክ የምርጫ ወረቀት እንዲላክልዎ ለመጠየቅ mnvotes.gov. ይጎብኙ

### ለመምረጥ ስለሚሰጥ ፍቃድ

*ከደሞዝዎ ምንም ሳቆረጥ፡ ከግል ፍቃድዎ ወይም ከዓመታዊ ዕረፍትዎ ሳይቀነስ ሂዶ ለመምረጥ ፍቃድ ማግኘት መብትዎ ነው።*

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE